# አዲሱ ጥምቀት

ተጠመቁ አለን ጌታ በወንጌሉ፤

የእዳ ሸክማችሁን እንድታቃልሉ።

ደግሞም አከለበት ጥብቅ ትዕዛዙን፤

አዋቂ ነውና እንዴት እንድንድን።

ጥምቀታችሁ ትሁን በተቀደሰ ውሀ፤

ከእቅፌ እንዳይወጣ ያ ምስኪኑ ድሀ።

በወተት አላልኩም አጥብቃችሁ ስሙ፤

ሀብታምና ድሀው በአንድ እንድትስማሙ።

በዘይት አላልኩም በሚያወዛ ቅባት፤

አይደለሁምና የሀብታም ብቻ አባት።

አላልኩም በሽቶ በባለ መዓዛ፤

ድሀ የት አግኝቶ በምኑ ሊገዛ?

እያለ ነገረን ብዙ አስተማረን፤

መጽሀፍ ጻፈልን በፍቅር ገሰጸን።

ታዲያ ዛሬ ደርሰን ስለምን ለወጥነው?

ከላይ እንደሁ አደል የሱ እማይሻርነው፤

ተወልዲያ ስንደርስ ትዕዛዝ የቀየርነው፤

ቅዱስ ውሀ ትተን በደም የጀመርነው?

በማሲንቆ ምትክ በከበሮ ፈንታ፤

ጥይት ተተኮሰ ክርስትያን ወደቀ አማራ ተመታ፤

ዕልልታ ቀረና ተተካ ኡኡታ፤

በሁለት ሺህ አስር በአምስተኛው ወር የሚካኤል ለታ።

የሰማዩን እንጃ በምድርስ ከፍቶናል፤

ብዙ አልቅሰናል አጽናኝም አጥተናል፤

ወይ ፍረድ ወይ ውረድ ብለን አማረናል።

ግና ምን ያረጋል ሠማይ ላይታረስ አንተም ላትከሰስ ነግረውናል አበው፤

እንደማትሳሳት ፍጹምነትህን በጠዋት ተረድተው።

እንግዲህ ፈጣሪ ወዳንተ ጮኸናል ፍረድልን ጌታ ብለን አልቅሰናል፤

ላረፉት ገነትን እንድትሰጥልን ተማምነንብሀል፤

መጽሀፍ ነግሮናል ደግሞም አይተነዋል፤

ፍርድና ምህረት በተመሳሳይ ቀን ከደጅህ ይቀዳል።

ታላቅ ተስፋችን ነው ጽኑ እንዲጨነቁ፤

ገዳይ እና አስገዳይ በዕጃችን ሊወድቁ።

አቤት የዚያን ግዜ አቤት የዚያን ለታ፤

ለተገፉን ሠናይ ለገዳይ የመርዶ ከበሮ ሲመታ፤

በዕልልታ ሲተካ የዛሬው ኡኡታ፤

የገዳይን ጓዳ ሲሞላው ሁካታ።

በ2010 የጥምቀት በዓል ላይ በወልዲያ በግፍ ለተገደሉት ወንድሞቼ